# የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

# የኢደ ምልክት አጠቃቀም መመሪያ

# ማውጫ


| ተራ ቁ. | ርዕስ | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 1 |
| 2 | ትርጓሜ | 2 |
| 3 | ወሰን | 4 |
| 4 | ዓላማ | 4 |
| 5 | የኢደ ምልክት ጠቀሜታ | 4 |
| 6 | የምልክቱ ባለቤትነት | 6 |
| 7 | የኢደ ምልክት ቅርፅ መለያዎች | 7 |
| 7.1 | የኢደ ምልክት ንድፍ፣አወቃቀርና መሰረታዊ ነገሮች | 7 |
| 8 | የምልክቱ የአጠቃቀም ደንብ | 8 |
| 8.1 | ምልክት አደራረግ | 8 |
| 8.2 | የምልክቱ አቀማመጥ | 9 |
| 9 | የኢደ ምልክት አሰጣጥ፣ እድሳት፣ እገዳና ስረዛ | 10 |
| 9.1 | የኢደ ምልክትን ለመጠቀም ስለሚሰጥ ፍቃድ እና ዕድሳት | 10 |
| 9.2 | እገዳ | 11 |
| 9.3 | የእገዳ የግዜ ገደብ | 12 |
| 9.4 | የፈቃድ ስረዛ | 12 |
| 10 | ምልክትን እንደገና ስለመጠቀም | 13 |
| 11 | የክትትል ሥራ | 13 |
| 12 | የፈቃድ የክፍያ ተመን | 14 |
| 13 | የደረጃ ምልክትን  በማስታወቂያ ወይም በማስታወቂያ ማቴሪያሎች ላይ ስለመጠቀም | 14 |
| 13.1 | ፈቃድን ስለማስተዋወቅ | 14 |
| 13.2 | የማስፋፋትና የማስተዋወቅ ሥራ አጠቃላይ መመሪያዎች | 15 |
| 14 | የባለፍቃዱ ግዴታዎች | 16 |
| 15 | የኢደ ምልክትን አላግባብ ስለመጠቀም | 18 |
| 16 | ቅሬታ እና ይግባኝ | 19 |
| 17 | ማጣቀሻዎች | 20 |

# በምርት ላይ ስለሚደረግ ብሔራዊ የደረጃዎች ምልክት አጠቃቀም መመሪያ

## (የኢ.ደ ምልክት ፍቃድ አሰጣጥ)

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ምልክት ከዚህ በኋላ “የኢ.ደ ምልክት” ተብሎ የሚጠቀሰው አንድ ምርት የተወሰነ የኢትዮጵያ ደረጃን ተፈላጊ ሁኔታዎች እና የሚመለከተውን ደንብ ወይም መመሪያ የሚያሟላ መሆኑን እና በዚህ መመሪያና በሚያረጋግጠው አካል መመሪያዎች ውስጥ በተገለፀው መሰረት ለተስማሚነት ምዘና መመሪያዎች ተገዢ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይኽም ምርቱ ተፈላጊ ሁኔታዎችን እንዲያሟላ በማድረግና ተአማኒነትን በመፍጠር በአገር ውስጥና በአለምአቀፍ ገበያ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ምልክቱ የሚያገለግለው አግባብነት ካለው የኢትዮጵያ ደረጃ ወይም በሚያረጋግጠው አካል ደንብ እና ተያያዥነት ያላቸው የማረጋገጫ ተፈላጊ ሁኔታዎች ውስጥ ከተጠቀሰ የኢትዮጵያ ደረጃ ጋር ለሚጣጣሙ ምርቶች ብቻ ነው፡፡

በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለፀው የኢ.ደ ምልክት አጠቃቀም መመሪያ በደንብ ቁጥር 193/2003 አንቀጽ 5 እና 14 መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ቀደም ሲል ምልክቱ አስገዳጅ ደረጃ ለነበራቸው ምርቶች ብቻ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ  በፍቃደኝነት እና በአስገዳጅነት ተፈፃሚ ለሆኑ የምርት ደረጃዎች ያገለግላል፡፡ በአምራቹ በኩል የኢ.ደ ምልክት በምርቶች ላይ የሚደረገው ምርቱ አግባብነት ያላቸውን የኢትዮጵያ ደረጃዎችና የቴክኒክ ደንቦችን በሙሉ ስለማሟላቱ ለመግለፅ ሲሆን በተስማሚነት ምዘና አካል ደግሞ ምርቱ ደረጃውን ስለማሟላቱ መረጋገጡን ለማሳየት ነው፡፡የተስማሚነት ማረጋገጫ ማመልከቻ

ለኢደ ምልክት አጠቃቀም ሲቀርብ ማመልከቻው ምርቱ ማሟላት የሚገባውን የምርት ደረጃ መስፈርት እና ተስማሚነቱን ለማረጋገጥ መሠረት የተደረገባቸውን ሌሎች መመሪያዎች ወይም ደንቦችን የያዘ ይሆናል፡፡

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ምልክትን (የኢደ ምልክት) በሁሉም የህትመትና የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ላይ ለመጠቀም አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ መረጃዎችን ይሰጣል፡፡ ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ምልክት ባለበት ሁኔታ ተጠብቆ እንዲቆይና ለህዝብ እንዲታወቅ ይረዳል፡፡ በሰርተፊኬት ሰጪው አካል በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚሰጥን የኢደ ምልክት አቀማመጥም ሆነ መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 በተገለፀው መሰረት ካልሆነ በስተቀር በምንም አይነት የጥበብ ሥራ መለዋወጥ አይቻልም፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

**"የተስማሚነት ምዘና"** ማለት ምርት፣ ሂደት፣ ስርአት፣ ሰው ወይም አካል፣ አግባብነት ያላቸውን ተፈላጊ ሁኔታዎች ማሟላቱን የሚሳይ ነው፤

**"የተስማሚነት ሰርተፊኬት"** ማለት አንድ ምርት ፣ሂደት፣ የአሰራር ስርአት፣ሰው ወይም አካል በተጠቀሰው ደረጃ ወይም ሌላ ማጣቀሻ ሰነድ ውስጥ የተቀመጡ ተፈላጊ መስፈርቶችን ስለማሟላቱ በተስማሚነት ምዘና አካል የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

**"የተስማሚነት ምዘና አካል (ተምአ)"** ማለት የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶችን የሚፈፅም አካል ነው፤

**"የኢትዮጵያ ደረጃ"** ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ የደረጃዎች አካል (በአሁኑ ወቅት ኢ.ደ.ኤ) እንደ ብሔራዊ ደረጃ የሚዘጋጅና በብሔራዊ የደረጃዎች ምክር ቤት የፀደቀ ብሔራዊ ደረጃ ማለት ነው ፤

**"ፈቃድ"** ማለት ፈቃድ አውጪው ተግባሩን በብቃት ማከናወኑን ለማሳየት ዕውቅና ባለው የተስማሚነት ምዘና አካል ለፈቃድ ጠያቂ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

**"ፈቃድ ያለው"** ማለት ውክልና ባለው የተስማሚነት ምዘና አካል የኢትዮጵያ የደረጃ ምልክትን ለመጠቀም ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ግለሰብ ማለት ነው፤

**"ሌብል"** ማለት የሚፃፍ፣የሚታተም፣እስቴንስል የሚደረግ፣ወይም የሚደጎስ፣በምርቱ መያዣ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ተለጣፊ ፣ልዩ የንግድ ምልክት፣ምልክት፣ስዕል ወይም ሌላ ገላጭ ነው፡፡

**"አስገዳጅ ደረጃ"** ማለት በህግ አስገዳጅ የሆኑ መሥፈርቶችን የያዘ ደረጃ ማለት ነው ፤

**"ብሔራዊ የደረጃ ምልክት (የኢ.ደ ምልክት)"** ማለት ምርቶች አግባብነት ካላቸው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር መስማማታቸውን ለማረጋገጥ የሚያገለግል የብቃት ማረጋገጫ ምልክት ነው፤

**"የምርት ሠርተፊኬሽን"** ማለት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ምልክት ያላቸው ምርቶችን መርምሮና በተገቢው የብሔራዊ ደረጃ ከተጠቀሱት ተገቢ መስፈርቶች ጋር ተስማሚ መሆናቸውን በማረጋገጥ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

**"ደረጃ"** ማለት ተግባራት ወይም ውጤቶቻቸው ለታለመላቸው ዓላማ ስኬታማ እንዲሆኑ ለጋራና ለተደጋጋሚ ጠቀሜታ የሚውሉ ህጎችን፣ መመሪያዎችን ወይም ባህሪያትን

የሚያስቀምጥ በስምምነት የተዘጋጀና ዕውቅና ባለው አካል የፀደቀ አግባብነት ያለው ሰነድ ነው (አይ ኤስ ኦ/አይ ኢሲ ጋይድ 2)፤

ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ወሰን

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ደረጃ በፈቃደኝነትና በአስገዳጅነት ተፈፃሚ የሚሆንባቸው በኢትዮጵያ ተመርተው የሚከፋፈሉ፣ወደውጭ የሚላኩና ወደ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን ያካትታል፡፡

## 4. ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

- የኢደ ምልክትን ለመጠቀም ፈቃድ የሚሰጥበትን ፣የሚታደስበትንና የሚሰረዝበትን ሁኔታዎች መደንገግ፤
- ምልክቱን በማስተዋወቅ በአምራቾች መካከል ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ፤
- በአገር ውስጥ የሚመረቱ እና ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የኢትዮጵያን ደረጃዎች ስለማሟላታቸው ለመፈተሽ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ፤

## 5. የኢደ ምልክት ጠቀሜታ

የኢደ ምልክት ለተጠቃሚዎች ወይም ለሸማቾች ምልክቱ የተደረገባቸው ምርቶች ተገቢ ከሆኑ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ተፈላጊ ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጫነት የሚውል አመላካች መሳሪያ ነው፡፡

- የኢደ ምልክት የምርቱ ተቀባይነት እንዲጨምር ይረዳል፡፡ ደንበኞች፣ አዲስ ሊመጡ የሚችሉ ደንበኞች ፣ ተቆጣጣሪዎች ፣ ቸርቻሪዎችና ነጋዴዎች የኢደ ምልክት የተደረገባቸውን ምርቶች ይመርጣሉ፡፡
- የኢደ ምልክት አዳዲስ ገበያዎች ውስጥ በቀላሉ ሰብሮ ለመግባት ያስችላል፡፡ የኢደ ምልክት በምርቱ ወይም በምርቱ ማሸጊያ ላይ፣ በምርቱ ማስታወቂያና ስለምርቱ በሚገልጽ ጽሑፍ ውስጥ መታየት በአዲስ የኢንዱስትሪ ዘርፍም ሆነ በአዲስ ዓለምአቀፍ ገበያ ውስጥ ምርቱ አዲስ ሊመጡ የሚችሉ ደንበኞች ጋር ለመድረስ ቀላል ያደርገዋል፡፡
- የኢደ ምልክት ፈጣን የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ ሰፊ መልእክት የሚያስተላልፍ ትንሽ ምልክት ነው፡፡
- የኢደ ምልክት ለማሻሻጫ የሚወጣውን ወጪ ይቀንሳል፡፡ በሶስተኛ ወገን መረጋገጡ ምርቱ በፍጥነት አስተማማኝና እርግጠኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡
- የኢደ ምልክት ሽያጭን ይጨምራል፡፡ይህ እውን ሊሆን የሚችለው በምልክቱ በዘላቂነት ለሚጠቀም፣ በህትመት ውጤቶች ለሚያሰራጭ፣ እንዲታይ ለሚያደርግ እና ምርቱ ይህን ውድ ምልክት ለመጠቀም ብቃት ያለው መሆኑን ለሚያስተዋውቅ ካምፓኒ ብቻ ነው፡፡
- የኢደ ምልክት ሸማቾችን ያነሳሳል፣ ደንበኞች እምነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
- የኢደ ምልክት የንግድ ጋሬጣዎችን ይቀንሳል፣ ፍትሃዊ የሆነ ውድድር እንዲኖር ያመቻቻል፡፡

- የኢደ ምልክት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጠቀሜታን ያስተዋውቃል፣ ለተግባራዊነቱም ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
- ሸማቾች የኢትዮጵያ ደረጃዎችን መስፈርት የሚያሟሉ ምርቶችን እንዲመርጡ በማስቻል የራሳቸውን ደህንነት እንዲጠብቁ ይረዳል፡፡
- የኢትዮጵያ ምርቶች በዓለምአቀፍ ገበያ ተአማኒነትና ተቀባይነት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

## 6. የምልክቱ ባለቤትነት

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ የምልክቱ የባለቤትነትን እና አጠቃቀሙን በተመለከተ የመወሰን መብት በደንብ ቀጥር 193/2003 ተሰጥቶታል፡፡ኢደ ምልክትን የመጠቀም ፍቃድ የመስጠት ሥልጣን በውክልና ለሚመለከተው ዕውቅና ላገኘ የተስማሚነት ምዘና አካል ይሰጣል፤ ይህም የሚሆነው ምልክቱን እንዲጠቀሙ ፈቃድ መስጠትን የተመለከተ መግባቢያ ሰነድ ላይ መሰረት ባደረገ ስምምነት ነው፡፡ የተወከለው የተስማሚነት ምዘና አካል ምርቶቻቸው ከተስማሚነት ምዘና አካሉ የብቃት ማረጋገጫ መመሪያዎች በተጨማሪ የተጠቀሱትን ደረጃዎች ፣ደንቦች ወይም መመሪያዎች ለሚያሟሉ፣ ብቁ ለሆኑ አምራቾች፣አስመጪና ላኪዎች በምልክቱ የመጠቀም ፍቃድ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

# 7. የኢደ ምልክት ቅርፅ መለያዎች

ምስል 1.የኢትዮጵያ ደረጃ (ኢደ) ምልክት

## 7.1 የኢደ ምልክት ንድፍ፣አወቃቀርና መሰረታዊ ነገሮች

የኢደ ምልክት የምርቱ ጥራት ወይም ደህንነት ተገቢነት ያላቸውን የኢትዮጵያ ደረጃዎች ድንጋጌ ያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ ያገለግላል፡፡ የተረጋገጠውን ምርት ለይቶ ለማወቅ እንዲቻል ደረጃውን እንደ መለያ በመውሰድ የኢደ ምልክቱ የኢደ ቁጥርን ይዟል፤ ይህም ምርቱ የሚያሟላውን ደረጃ በቀላሉ ፈልጎ ለማግኘት ያስችላል፡፡ የኢደ ምልክት ሁለት ክፍል ሲኖረው ይኸውም ፊደላዊ ቅንብር (ሞኖግራም) እና አግባብነት ያለው የኢትዮጵያ ደረጃ ማጣቀሻ ነው፡፡ በባለፍቃዱ ጥቅም ላይ መዋል የሚችለው ተመራጩ የፊደላዊ ቅንብር (የሞኖግራም) መጠን ከታች ተሰጥቷል፡፡ ነገር ግን በልዩ ሁኔታዎች በፎቶግራፍ ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ መቀነስ ወይም ማሳደግ ይፈቀዳል፡፡

ምልክቱ ቢያንስ 0.5 ሴሜ ርዝመትና 0.5 ሴሜ ከፍታ ይኖረዋል፡፡በተስማሚነት ምዘና አካል የሚሰጠው መለያ ኮድ ምስሉ ላይ በተመለከተው ሳጥን ውስጥ ይቀመጣል፡፡ የመለያ ኮዱ የፊደል መጠን አላስፈላጊ ከፍታ ሳይጨመርበት በተጠቃሚዎች መለየት መቻል አለበት፡፡

በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር እነዚህ መሰረታዊ ነገሮች በሙሉ በአንድነት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡ የኢደ ምልክት ቅጂ በሙሉ ኤጀንሲው በወሰነው የልኬ-ቅርፅ መጠን እና የቀለም አይነት ጋር የተጣጣመ መሆን አለባቸው፡፡

## 8. የምልክቱ የአጠቃቀም ደንብ

### 8.1 ምልክት አደራረግ

የኢደ ምልክት ለመጠቀም ፍቃድ ያለው ምልክቱን ፍቃድ ባላቸው ምርቶች ላይ ለመጠቀም መብት ተሰጥቶታል፡፡ ምልክቱም ዘላቂና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ፣ምርቱ ሳይጎዳ ደረጃው ላይ በተገለፀው ሁኔታና ቦታ ላይ  መደረግ አለበት፡፡ በተቆጣጣሪው አካል ደንብ ወይም መመሪያ ካልተገለፀ በስተቀር የኢደ ምልክት ከባለፍቃዱ አርማ (ሎጎ) ወይም የንግድ ምልክት ጎን መቀመጥ አለበት፡፡ በምልክት የሚጠቀሙ ምርቶች በተለያዩ የብዙሀን መገናኛዎች ለህዝብ በሚገለፁበት ወይም ማስታወቂያ ሲሰራላቸው ምልክቱ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

የኢደ ምልክት ቀጥታ በእያንዳንዱ ምርት ላይ ወይም ይህ ካልተቻለ በማሸጊያው ላይ መደረግ አለበት፡፡ምልክቱ ምርቱ የተረጋገጠበትን የምርት ደረጃ ቁጥር የያዘ መግለጫ ይይዛል፡፡ የኢደ ምልክት የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል፡-

- የኢደ ምልክት ፊደላዊ ቅንብር (ሞኖግራም)፣
- የተወሰነው የደረጃ ቁጥር፣
- እንደአስፈላጊነቱ መደብ ወይም ደረጃ፣
- የማረጋገጫ ሰርተፊኬት ቁጥር

## 8.2 የምልክቱ አቀማመጥ

- ፊደሎቹና መለያ ኮዱ በሚገባ ተነባቢ እስከሆኑ ድረስ ምልክቱ በተመሳሳይ ቅርፅና ሬሾ ሊያድግ ወይም ሊቀንስ ይችላል፤ ሆኖም አጠቃላይ ልኩ-ቅርፁ ከ0.5×0.5 ሴሜ ማነስ የለበትም፡፡
- የምልክቱ ቀለም ምስል 1 ላይ የተመለከተው ነው፡፡ ከሚያረጋግጠው አካል ጋር ስምምነት ከተደረሰ በነጭ መደብ ላይ ጥቁር መስመሮችን መጠቀም ይፈቀዳል፡፡ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ ምልክቱ በሚገባ የሚነበብ መሆን አለበት፡፡
- የምልክቱ ቀለም ሰማያዊ እና ቀይ ነው፡፡
- የምልክቱን ቀለም ማሻሻል አይፈቀድም፡፡
- ምልክቱን በምርቱ ማሸጊያ ላይ ማድረግ ይቻላል፡፡
- በህጋዊ የኢደ የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ውስጥ ያልተካተቱ ምርቶች ዝርዝር በያዙ ካታሎጎች ወይም ድረ-ገፅ ውስጥ ምልክቱን መጠቀም አይፈቀድም፡፡

## 9. የኢደ ምልክት አሰጣጥ፣እድሳት፣እገዳና ስረዛ

### ማመልከቻ ስለማቅረብ

ማንኛውም በኢትዮጵያ ደረጃ ምልክት ለመጠቀም ፍቃድ ለማግኘት የሚገደድ ወይም የሚፈልግ የአገር ውስጥ አምራች፣ ላኪና አስመጪ በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ኃላፊነት ለተሰጠው ለተገቢው የተስማሚነት ምዘና አካል ጥያቄውን ማቅረብ ይኖርበታል።

ሥልጣን የተሰጠው የተስማሚነት ምዘና አካል የሚከተሉትን መመሪያዎች ማዘጋጀት አለበት ፦

- የማረጋገጫ ሰርተፊኬት አሰጣጥ ስርዓት፣
- ፍቃድ ለማግኘት የጥያቄ አቀራረብ ስርዓት፣
- የፍቃድ አሰጣጥ ስርዓት፣
- ፍቃድ ለመስጠት ወይም ለማደስ የሚጠየቁ የክፍያ ተመኖችን በኤጀንሲው የማፀደቂያ ስርዓት፣

### 9.1 የኢደ ምልክትን ለመጠቀም ስለሚሰጥ ፍቃድ እና ዕድሳት

9.1.1 የኢደ ምልክትን ለመጠቀም ፍቃድ የሚሰጠው የተስማሚነት ምዘና አካል በመጀመሪያው ምዘና አመልካቹ ባለው ተፈላጊ ችሎታ፣መሳሪያዎች፣የአሰራር ስርዓትና ሀብት የረካ እና አግባብነት ያለውን የኢትዮጵያ ደረጃ የሚያሟላ ምርት ለማምረት ብቃት እንዳለው ካመነ፣

9.1.2 ፍቃዱ ለመጀመሪያ ግዜ ለአንድ አመት ይሰጣል።

9.1.3 የተስማሚነት ምዘናው አካል ፍቃዱ እንዲታደስ ያደርጋል፣

9.1.4 ባለፍቃዱ ተፈላጊ ሁኔታዎችን የሚያሚላ ከሆነ ፍቃዱ ለተጨማሪ ሁለት ዓመት ሊታደስለት ይችላል፡፡

9.1.5 በደረጃዎች ምልክት ለመጠቀም ፍቃድ ሲሰጥ ለኢደኤ ማሳወቅና በመንግሥታዊ ጋዜጣ ላይም መገለፅ አለበት፡፡

## 9.2 እገዳ

9.2.1 ባለፍቃዱ ጥያቄ ሲያቀርብ በተስማሚነት ምዘና አካል ፍቃዱ ሊታገድ ይችላል፡፡

9.2.2 እንደ የጎርፍ አደጋ፣ የእሳት ቃጠሎ፣የመሬት መንቀጥቀጥ እና በመሳሰሉት አደጋዎች ወቅት፣

9.2.3 ባለፍቃዱ ሥራ ማቆሙን ሲያሳውቅ፣

9.2.4 በፍርድ ቤት ወይም በህግ ኃላፊነት በተሰጠው አካል ሥራው እንዲዘጋ ሲታዘዝ ፣

9.2.5 በተስማሚነት ምዘና አካል ፍቃዱ ሲታገድ

9.2.6 በማስታወቂያዎች ላይ አሳሳች ህትመቶች ማስፈርን የመሳሰለ ህገወጥ የሆነ የደረጃ ምልክት አጠቃቀም ሲፈፀም በአካባቢው ተገቢ የሆነ መፍትሄ እርምጃ ካልተወሰደ፣

9.2.7 በተገቢው የኢትዮጵያ ደረጃ ውስጥ ላልተካተተ ምርት የደረጃ ምልክት መጠቀም፣

9.2.8 ተጠቃሚው ተፈላጊ መረጃዎችንና ናሙናዎች ሥልጣን ለተሰጠው ኢንስፔክተር ማቅረብ ሳይችል፣

በደረጃ ምልክት የመጠቀም ፈቃድ በተስማሚነት ምዘና አካል ሊታገድ ይችላል።

ሆኖም የምርቱ ከኢትዮጵያ ደረጃ ተፈላጊ ሁኔታዎች ጋር አለመጣጣም ዝቅተኛ ከሆነ ወይም የተከናወነው ፍተሻ ውጤት ይህንን የሚያሳይ ከሆነ ወዲያው ፍቃድ መሰረዝ አስፈላጊ አይሆንም።

## 9.3 የእገዳ የግዜ ገደብ

ከመስፈርቶች አለመጣጣም ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተስተካከሉና ካልታረሙ ፈቃዱ እንደታገደ ይቆያል።

## 9.4 የፈቃድ ስረዛ

የሚከተሉት ሁኔታዎች ተሟልተው ካልተገኙ የተስማሚነት ምዘና አካሉ ፈቃዱን ሰርዞ ለኢደኤ ማሳወቅ ይኖርበታል።

9.4.1 ተጠቃሚው የአገልግሎት፣የምርመራ እና የድጋሚ የማረጋገጫ ሰርተፊኬሽን ክፍያ ካልፈፀመ፣

9.4.2 ተጠቃሚው ከከሰረ፣ድርጅቱን ከዘጋ ወይም ምርት ማምረት ካቆመ፣

9.4.3 በእገዳው ወቅት ተጠቃሚው በቂ የሆነ የእርምት እርምጃዎች ካልወሰደ፣

9.4.4 በተሰጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ፈቃዱን ሳያሳድስ ሲቀር ወይም ሌሎች ከፈቃዱ ጋር የተገናኙ በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱ መስፈርቶችን ሳያሟላ ሲቀር፣

9.4.5 ደረጃዎቹ ወይም ደንቦቹ ሲለወጡና ተጠቃሚው አዲሶቹን ተፈላጊ ሁኔታዎች ማሟላት የማይፈልግ ወይም የማያሟላ ከሆነ፣

9.4.6 በተደረገው ክትትል የታየው ከተፈላጊ ሁኔታዎች ጋር አለመጣጣም ከፍተኛ መሆን።

## 10. ምልክትን እንደገና ስለመጠቀም

10.1 አንድ የታገደ ወይም የተሰረዘ ፈቃድ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ ከተወሰደና ምርቱ ተገቢውን ደረጃ / ቴክኒካዊ ደንቦችን ያሟላል ተብሎ ከተረጋገጠ በምልክቱ እንደገና እንዲጠቀም ይፈቀድለታል።

10.2 ይህንንም ተስማሚነት ምዘና አካሉ እንደገና መግለፅ እና ለኢደኤ ማሳወቅ አለበት።

## 11. የክትትል ስራ

11.1 ፈቃድ የተሰጠው ምርት በቀጣይነት ተገቢዎችን የኢትዮጵያ ደረጃዎች ስለማሟላቱ ለማረጋገጥ የማያቋርጥ ክትትል መደረግ አለበት።

11.2 ክትትሉም በአይኤሶ/አይኢሲ 17065 አንቀፅ7.9 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።

## 12. የፈቃድ ክፍያ ተመን

የፈቃድ ክፍያ በተስማሚነት ምዘና አካል የሚወሰን ሆኖ ስልጣን በተሰጠው አካል የሚፀድቅ ይሆናል ። ሆኖም ክፍያው ተመጣጣኝና ያልተጋነነ መሆን አለበት።

ለኤጀንሲው የሚደርሰውን የገቢ መጠን አስመልክቶ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ከተስማሚነት ምዘና አካሉ ጋር በሚደርገው የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ መሠረት ሊሆን ያችላል።

## 13. የደረጃ ምልክትን በማስታወቂያ ወይም በማስታወቂያ ማቴሪያሎች(ቁሳቁሶች) ላይ ስለመጠቀም

### 13.1 ፈቃድን ስለማስተዋወቅ

ባለፍቃዱ የኢደ ምልክትን ለመጠቀም ፍቃድ የተሰጠው መሆኑን ለደንበኞቹ በመገናኛ ብዙሀን ማስተዋወቅ ይችላል።

- ፈቃድ የተሰጠው አምራች ወይም አቅራቢ ሠርተፊኬት ላገኘባቸው ምርቶች የኢደ ምልክትን ለመጠቀም ፍቃድ ያለው መሆኑን የማስተዋወቅ መብት አለው። የማስተዋወቅ ሥራ የሚከናወነው የማምረት ሥራው ከተጠናቀቀና የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ብቻ ነው።
- ምልክቱ በማስታወቂያ ላይ የሚውለው ተገቢ በሆነ የኢትዮጵያ ደረጃ ለተሸፈኑና በሰርተፊኬሽን አካሉ የኢደ ምልክት የፍቃድ አሰጣጥ የግዜ ሰሌዳ ላይ ለተዘረዘሩ ምርቶችን ብቻ ነው። ማረጋገጫ ያላቸው ምርቶች

ማረጋገጫ ከሌላቸው ጋር በሚተዋወቁበት ወቅት ፍቃድ ያለው አምራች ወይም አቅራቢ በማያሳስት መልኩ ልዩነታቸውን መግለፅ ይኖርበታል፡፡ የማስታወቂያው ሥራ የኢደ ምልክት ያላቸውና የሌላቸው ምርቶች በማይደባለቁበት አኳኋን መከናወን አለበት፡፡

- ፍቃድ ያለው አምራች ወይም አቅራቢ የተመረቱት ወይም የቀረቡት ምርቶች የተወሰኑትን ደረጃዎች እንደሚያሟሉ ለማሳየት በህንፃው ላይ የማስታወቂያ ሰሌዳ ሊሰቅል ይችላል፡፡

- የደረጃ ምልክቱ ለማስታወቂያ ሲውል የተሟላ ሊሆን የሚችለው ተገቢውን የሰርተፊኬት ቁጥር ከያዘ ብቻ ነው፡፡

- ከአንድ ምርት በላይ ማስታወቂያ የሚሰራለት ከሆነ ለእያንዳንዱ ምርት የደረጃ ምልክቱ ከሰርተፊኬት ቁጥር ጋር መሆን ይኖርበታል፡፡የቦታ ጥበት ከተከሰተ አንድ የደረጃ ምልክት ሊደረግ ይቻላል፡፡

## 13.2 የማስፋፋትና የማስተዋወቅ ሥራ አጠቃላይ መመሪያዎች

- ማናቸውም የኢደን ምልክት በማጣቀስ የሚሰሩ የማስታወቂያ ሥራዎች የተሟሉና ትክክል መሆን አለባቸው፡፡

- ምርቱ በኢትዮጵያ ደረጃዎች የተዘረዘረ ፣የተመደበ፣በተግባር የተረጋገጠ ወይም የታወቀ መሆኑ በትክክል መገለፅ አለበት፡፡

- የኢደ ምልክት በማንኛውም ሁኔታ ምርቱን ከሚያመርተው ወይም ከሚሸጠው ካምፓኒ ስም በላይ ጎልቶ በማስታወቂያ ወይም በማሸጊያ ላይ መታየት የለበትም፡፡
- በኢትዮጵያ ደረጃዎች መሰረት ያልተፈተሹ የሌላ ድርጅቶች ሠርተፊኬሽን ያላቸው ምርቶች የኢደ ምልክትን መጠቀም አይችሉም፡፡
- በድረ-ገፃቸው ላይ የኢደ ምልክትን የሚጠቀሙ አካሎች የኢደ ምልክት ለመጠቀም ሰርተፊኬት ያገኙትንና ሰርተፊኬት ያላገኙትን ምርቶች ጎብኝዎች በግልፅ ለይተው እንዲያውቋቸው ማድረግ አለባቸው፡፡
- የምርት ሰርተፊኬሽንን ለመግለፅ አገልግሎት ላይ የዋለ የኢደ ምልክት እና ማንኛውም አባሪ ምስል፣ምልክት ወይም ቃል በደንበኞች በግልፅ መታወቅ ወይም መነበብ በሚችል መጠን ጎልቶ መታየት ይኖርበታል፡፡
- በኢትዮጵያ ደረጃዎች ያልተረጋገጡ ምርቶችን በያዙ ማሸጊያዎች ላይ የኢደ ምልክት አይደረግም፡፡

## 14. የባለፈቃዱ ግዴታዎች

**ባለፈቃዱ**

- ፈቃድ ባገኘባቸው ምርቶች ማሸጊያ ፣በምርቱ ፣ቅድመ እሽጋት ባላቸው ምርቶች ሌብል እና/ ወይም በክምችት ማሸጊያ ማቴሪያሎች ላይ የኢደ ምልክትን ማድረግ አለበት፡፡

- በህገወጥ መንገድ የኢደ ምልክት ወይም ተመሳሳይ ምልክቶች የተደረገባቸው ምርቶችን እያወቀ መሸጥ፣ ማሳየት፣ ማከማቸት፣ማጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የለበትም፡፡

- የደረጃ ምልክቱን አስመስሎ መስራት፣ምልክቱን ለመቀየር መነካካት፣አቀማመጡን መቀየር፣መግዛት ፣መሸጥ ወይም ለሌላ ማስተላለፍ አይችልም፡፡

- የተስማሚነት ምዘና አካል ኢንስፔክተሮች በህግ በተወሰነው የስራ ሰዓት የተስማሚነት ምዘና ተግባራቸውን ለማከናወን ወደድርጅቱ እንዲገቡ መፍቀድ አለበት፡፡

- ፈቃድ ከተሰጠው ከሶስት ወራት በኋላ ስራውን የሚያቋርጥ ከሆነ ለተስማሚነት ምዘና አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

- የኢደ ምልክትን በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት መጠቀም አለበት፡፡

- ለተስማሚነት ምዘና ተግባር የሚውሉ ናሙናዎችን ማቅረብ አለበት፡፡

- ምርቶች ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር ተጣጥመው እንዲቀጥሉ ለማስቻል ብቁ የሆነ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

- የኢትዮጵያ ደረጃዎችን /የቴክኒካዊ ደንብ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ሙሉ በሙሉ ለሚያሟላ(ሉ) ምርቶች ብቻ የኢደ ምልክት መጠቀም አለበት፡፡

## 15. የኢደ ምልክትን አላግባብ ስለመጠቀም

ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የኢደ ምልክትን መጠቀም የተከለከለ ነው፡-

- የሰርተፊኬሽን አሰጣጥ ስርዓቱ በሂደት ላይ ከሆነ ፣
- በሰርተፊኬቱ ላይ የተጠቀሰው ምርት ለውጥ ወይም ማሻሻያዎች ከተደረጉበት እና የተስማሚነት ምዘና አካል ውሳኔ ያልሰጠባቸው ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ለውጦች ያልተገመገሙ ወይም ያልተገለፁ ከሆነ፣
- በማንኛውም ምክንያት የተሰጠው ፈቃድ የተሰረዘ ከሆነ፣
- ፈቃድ ያገኘባቸውን ውስን ምርቶች በመጠቀም ምርቶቹ በሙሉ ፍቃድ ያላቸው አስመስሎ በማስተዋወቅ ተመልካችን ማሳሳት፣
- ፍፁም ፍቃድ ባልተሰጣቸው ምርቶች ላይ ምልክቱን መጠቀም፣
- ከሚመለከተው የተስማሚነት ምዘና አካል በቅድሚያ በፅሑፍ ስምምነት ሳይረጋገጥ የኢደ ምልክትን ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ወይም እንዲጠቀምበት መፍቀድ፣
- ምርቱ ፍቃድ ያገኘበት ደረጃ የተሻረ፣የተሻሻለ ወይም አዲስ ዕትም የተዘጋጀለት ከሆነ እና ምርቱም በዚሁ መሠረት ወቅታዊ ሰርተፊኬት ከሌለው፣
- በካምፓኒው የፅሕፈት መሳሪያዎች ፣ የአድራሻ መግለጫ ካርዶች ወይም ምልክቶች ላይ መጠቀም ፤

## 16. ቅሬታ እና ይግባኝ

- ባለፍቃዱ ላቀረበው ቅሬታ በተሰጠው ውሳኔ ካልረካ ለኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡
- የተስማሚነት ምዘና አካሉ የቅሬታና የይግባኝ አቀራረቡ ስርዓቱን በአይኤስኦ/አይኢሲ 17065፡2012 መሠረት ማከናወን አለበት፡

## 17. ማጣቀሻዎች


- በአይኤስኦ/አይኢሲ 17030 - ለሶስተኛ ወገን የተስማሚነት ምልክቶች ጠቅላላ ተፈላጊ ሁኔታዎች፣
- በአይኤስኦ/አይኢሲ 17065 - ለምርቶች ፣ ለሂደቶችና ለአገልግሎቶች ሰርተፊኬት ለሚሰጡ አካላት ተፈላጊ ሁኔታዎች፣
- የሰርተፊኬት ደንብ - የህንድ የደረጃዎች ቢሮ
- የተስማሚነት ፕሮግራም ምልክትን ለመተግበር የሚያገለግሉ ደንቦች

  የእስራኤል የደረጃዎች ኢንስትትዩት፣2ኛ ዕትም -ማርች 1995